**ኢትዮጵያና የሩቅ ምስራቅ እስያ አገሮችን የልማታዊ መንግስት ሞዴል የመከተል ተግዳሮቶች—ታዲያ ምን አማራጭ አላት?**

**ከድልበቶ ደጎዬ ዋቆ**

እንደእኔ ግንዛቤና ትዝብት፣ የኢህአዴግ የፖለቲካ ርእዮተአለምና የኢኮኖሚ እድገት ሞዴል "የእስያ ነብሮች" ተብለው የሚታወቁት የሩቅ ምሥራቅ እስያ አገሮች(ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን፣ ሲንጋፖር፣ ቻይና፣ ወዘተ) ናቸው። የአፄ ሃይለስላሴ ንጉሳዊ ስርአትም ለመከተል ሞክሮ ሳይሳካለት የጨነገፈው የዘመናዊነት ሞዴል የምእራቡን ሳይሆን የጃፓንን ነበር፣ የሚያስገርም  የገዥዎቻችን የሚጣጣም ዝንባሌና ምኞት!።

ይህንን በዚህ አቁመን ወደርእሰ—ጉዳያችን ስንመለስ፣ ቻይና በአንድ የኮሙኒስት ፓርቲ የምትመራ (ዴሞክራሲያዊ ዲክታተርሽፕ) አገር ስትሆን ኮሪያና ታይዋን ነፃና ፍትሃዊ ምርጫዎችን በየተወሰኑ አመታት እያካሄዱ በሚመሰረቱ መስተዳድሮች የሚመሩ የብዙሃን ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ አገሮች ናቸው። የልማታዊ መንግስት (developmental state) ሞዴል የተመረጠበት አቢይ ምክያንትም፣ በእንዱስትሪ እድገት ረገድ እጅግ ወደኋላ የቀሩት ታዳጊ አገሮች እጅግ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ከድህነት አረንቋ ባጭር ጊዜ እንዲወጡ ከተፈለገ በሥልጣን ያለው አውራ ፓርቲና መንግሥት ትክክለኛ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና እስትራተጂዎችን በመንደፍ እንዲሁም ቴክኖክራቲክ የሆነና የሙያ ክህሎት ያለው፣ ከሙስና የፀዳና በስነምግባር የታነፀ ቢሮክራሲ በማስፈን በኢኮኖሚው ዘርፍ በቀጥታ ጣልቃ በመግባትና በእርሻ—መር እንዱስትሪያላይዜሽን ተልእኮ ወሳኝ ሚና በመጫወት ለኢኮኖሚ እድገት ሲባል አገሪቱን ማናቸውንም ዋጋ እንድትከፍል በማስገደድ ወደዘላቂ የእድገት ጎዳና ካላስገባ ለረጅም ዘመን ደካማ ሆኖ የቆየው የግሉ ዘርፍ ይህንን የኢኮኖሚ እድገት የማሳለጥና የማፋጠን ሚና ለመጫወት አቅም የለውም ከሚል ትክክለኛ ግንዛቤ በመንደርደር ነው። በዚህ ረገድ እስቲ ቻይናን እንደምሳሌ ወስደን እንመልከት። እንደሚታወቀው ቻይና በቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ የተማከለ አመራር የሚዘወር "ዴሞክራሲያዊ ዲ   ታተርሽፕ" ወይንም አምባገነናዊ ኮሙኒስታዊ አገዛዝና (የሕግ አውጪ፣ የስራ አስፈፃሚ ቅርንጫፍ ይሐውም የመንግሥት ምክር ቤት እና የፍትህ አካል፣ ወዘተ) ያላት ሲሆን የሬፑብሊኩ ኮሙኒስታዊ ህገመንግስት በሚደነግገው መሠረት እነዚህን አካላትና የሚዲያ ተቋም እንዲሁም የነፃ አውጪ ሠራዊቱን በሚሊተሪ ኮሚሽን አማካኝነት በቀጥታ የሚቆጣጠረው የኮሙኒስት ፓርቲው ፖሊትቢሮና ፕሬዚዳንቱ ነው።  የቻይና ህዝብ 95% የአንድ ብሄር ይሐውም የሃን (Han) ብሄር የበላይነት የነገሰበት፣ የአገሪቱን 5% የሕዝብ መጠን የሚሸፍኑት ከ56 የማያንሱ ማይኖሪቲ (አናሳ) ብሔረሰቦች ተበታትነው የሚኖሩባት አገር ስለሆነች ያለአንዳች ተገዳዳሪና ፈታኝ ተቃውሞ በአንድ የተማከለ ኮሙኒስት ፓርቲ አመራርና ማእከላዊ የኢኮኖሚ ፕላን ኮሚሽን በመመራት ከ1980 (እኤአ) ጀምሮ ግን የፖለቲካ ስርአቱ ሳይለወጥ የኢኮኖሚ ሴክተሩን ወደነፃ የገበያ አኮኖሚ ሥርአት ሊበራላይዝ ወይንም ሪፎርም በማድረግ በአጭር አመታት እጅግ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብና ከ100 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ከድህነት ሰቆቃ በማላቀቅ የአለም ሁለተኛ ግዙፍ የኢኮኖሚና የሚሊተሪ ባለቤት ለመሆን በቅታለች።

ኢትዮጵያ የቻይናን አይነት የእድገት ሞዴል ለእርሷ በሚበጅ ሁኔታ በማሻሻል ገቢራዊ ለማድረግ ብትሞክር እንኳ የተማከለ የፓርቲና የአስተዳደር አመራር ለመከተል እንዳትችል የሚያደርጉ ግልፅ ተግዳሮቶች ተደቅነውባታል፣ ይሐውም እንደቻይናው የሃን ብሄር ከሌሎች ብሄሮች ሁሉ በወሳኝነት ብልጫ ያለው ቀርቶ ከአገሪቱ ህዝብ ከግማሽ በላይ የሆነ(50%+ ) አንድም ብሄር በኢትዮጵያ አይገኝም፣ በአሃዝና በመቶኛ ስሌት ከአነስተኛ እስከከፍተኛ የሚበላለጡ ቢሆንም ሁሉም  ማይኖሪቲ (አናሳ) ብሔሮች/ብሄረሰቦች ናቸው፣ ሁሉም እኩልነታቸውን አስጠብቀው ፍትህ በሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት ስር ለመኖር የሚሹና እንዳለፉት ዘመናት በማንም የሌላ ብሄር (አናሳም ሆነ አብላጫ ብሄር) ልሂቃን ገዥ መደብ ቁጥጥርና የበላይነት ስር በጭቆና ለመገዛት አይሹም ። በዚህም የተነሳ አንድ አገርአቀፍ ውሁድ አውራፓርቲ ካልተፈጠረ በስተቀር እጅግ የተማከለ ኮሙኒስታዊ/አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥትና የፓርቲ  አመራር ለመዘርጋትና ለመቆጣጠር አዳጋች ይሆናል። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ያለን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ  አውራ ፓርቲ/ኢህአዴግ/ ከ1993 አም የህወሃት የውስጥ ክፍፍልና ቀውስ ወዲህ በተለይ ደግሞ ከጠቅላይ ሚኒስትርና የኢህአዴግ ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ ሞት ቀጥሎ ባሉት አመታት በአገር አቀፍ

ደረጃ እንደቀድሞው በርእዮተአለምና በአሰራረ የተዋሃደና ውጤታማ የሆነ አንድ ጠ  ካራ ማእከላዊ አመራር ሊዘረጋ ያልቻለ ከመሆኑም በላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይባስ ከከፍተኛ አመራር አንስቶ እስከታችኛው እርከኖች ድረስ በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ ተቋማት፣ ወዘተ ደረጃዎች ሁሉ በሙስና፣ በኪራይ ሰብሳቢነትና በብልሹ አሰራሮች ከመበከሉም በላይ በተዛባ የስልጣንና የሀብት ክፍፍል ግጭቶች ሳቢያ እርስ በእርስ የሚናቆሩ አራት አባል ድርጅቶች የሚሳተፉበት አስተማማኝ ያልሆነ የጥምረት (coalition party and government ) ፓርቲና መንግሥት (መስተዳድር) ሆኖ በተዳከመ ሁኔታ እያዘገመ ይገኛል፣ "የማይተማመኑ ባልንጀራሞች በየወንዙ ይማማላሉ"፣ እንዲሉ የፖለቲካ ስልጣን ጡንቻ ከ1983 አም አንስቶ በወሳኝነት ወደህወሃት ያጋደለ መሆኑ በሌሎቹ አባል ድርጅቶች ዘንድ እያደር ቅሬታዎችን ከማሳደሩም በላይ የውስጥም ሆነ የውጭ ዴሞክራሲያዊ ውህደት እጦት የሚያጠቃው የአራት አባል ድርጅቶች ልል የጥምረት ፓርቲ ሊሆን ተገድዷል። ይባስ ደግሞ የቻይናንና የሩቅ ምስራቅ ነብሮችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ እድገት ሞዴል ፍፁም በሚቃረን ሁኔታ የዘውግ ፌደራሊዝምን (ethnic-based federalism) ተግባራዊ ያደረገ፣ እያንዳንዱ ብሔር ያለአንዳች ገደብ ባሻው ጊዜ ለመገንጠል እንዲችል የሚፈቅድ፣ የተባበሩት መንግስታት መንግስታት ማህበር እንደኤአ በ1948 ያፀደቀውን የሰብአዊ መብቶች ዴክለራሲዮንና የአፍሪካ ህብረት የህዝቦችና የግለሰቦች መብቶች ቻርተር፣ ወዘተ የሚቀበል ሊበራል ሕ  መንግሥታዊ ስርአት የዘረጋ አገዛዝ/ መንግስት ነው ኢትዮጵያ ያላት። ከሞላጎደልም ቢሆን የቻይናን ሞዴል በመከተል አገራችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት መንጭቀን ለማስወጣት እንችላለን ከተባለ ቻይና እንዳደረገችው ሁሉ ጠንካራና የተማከለ የአንድ አውራ ፓርቲ አመራር በማስፈንና ማእከላዊ የኢኮኖሚ እቅድ በመተለም፣ ቴክኖክራቲክ የሆነና ከሙስና የፀዳ የመስተዳድር ቢሮክራሲ በመገንባትና በስነምግባር የታነፁና በክህሎት የተካኑ የሲቪል ሰርቪስ ባለሙያዎችን በማሰለፍ በቆራጥነት ለመታገልና ሕዝባችንን ከድህነት በአጭር አመታት ጊዜ ውስጥ ለማላቀቅ ወሳኝ እርምጃዎችን ለመውሰድ እንችላለን ብሎ ማሰብ በሃሳብ ደረጃ ተቀባይነት ያለውና አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎች ለዚህ ታላቅ አላማ አመቺ ናቸው ወይ ብሎ መጠየቅ ይገባል። ተጨባጭ ሁኔታዎች አጋዥ ሚና የማይጫወቱ ባይመስልም የቻይናን የእድገት ሞዴል የግድ መከተል አለብን ከተባለና በዚህ እቅድ ከተስማማን የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ህልውና ያከትማል፣ ከነርሱ ጋር የሚደረገው ውይይትና ድርድርም ጉንጭአልፋ የጊዜ መግዣ ታክቲክ ከመሆን አያልፍም። ምክንያቱም ባጭሩ፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮተአለም ከእርሱ አስተሳሰብ ያፈነገጡ ነፃ ተቋማትና የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲኖሩ በፍፁም አይፈቅድምና፣ "ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት በፊትህ አይኑሩ፣" እንደተ  ለው የኦሪት ትእዛዝ የኢህአዴግ ግንባር ፓርቲም የሚመራበት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ቀኖናዊ ርእዮተአለም ከኢህአዴግ ውጭ ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖችና ነፃ ተቋማት እንዲኖሩ በጭራሽ አይፈቅድም።

በሌላው አንፃር፣ የተቀሩትን የእስያ "ነብሮችን" የብዙሃን ፓርቲ ዴሞክራሲና የነፃ ገበያ ስርአትና ካፒታሊስታዊ የእድገት ሞዴል የምንከተል ከሆነ በቅድሚያ የግብርና አብዮት በማሳካት አብዛኛውን አርሶአደር ህዝብ የመግዛት አቅምና የሀገር ውስጥ ገበያ በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ የአርሶአደሩን መደብ በወሳኝነት ወደከተሜነትና ወደደመወዝ ተቀጣሪነት እንዲሸጋገር በማድረግ የመደብ ጥቅሞችና ፍላጎቶችን የሚወክሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩ በማብቃት በዚህ መንገድ እስትራክቸራል ትራንስፎርመሽን ማካሄድ የማይታለፍ እስትራተጂ መሆን ነበረበት፣ ይህንን ሳናሳካ የእንዱስትሪያላይዜሽን እድገት ብቻ ለማሳለጥ ሲባል የውጭ ኢንቨስተሮችን መጋበዛችንና የእንዱስትሪ ፓርኮችን በየቦታው መትከላችን እጅግ አስፈላጊ ቢሆንም በዚህ አቅጣጫ ብቻ ማተኮሩ ለውጭ ብዝበዛና ለካፒታል ሽሽት (capital flight) የሚዳርገን አደገኛ እስትራተጂ ስለሆነ የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮችን እጅግ ጠቃሚ ሚና የሚያዳክም እንዳይሆን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ የግድ ይሆናል። መታወቅ ያለበት ቁምነገር፣ የውጭ ኢንቨስተሮች በዝቅተኛ ወጭ ከፍተኛ ትርፍ አግበስብሰው ማናቸውም የፖለቲካ አለመረጋጋት በሀገራችን ውስጥ ከተከሰተ ያለአንዳች ማመንታት አገሪቱን ጥለው የሚሸሹ ዘራፊና አስተማማኝ የልማት አጋሮች ሊሆኑ የማይሹና የማይችሉ የቻይና  የመካከለኛው ምስራቅ አረብ አገራት፣ የቱርክ፣ የህንድ፣ የግብፅ፣ የአውሮፓ አገራት፣ ወዘተ ኩባንያዎች መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። በተጨማሪ፣ የእንዱስትሪ ፓርኮቻችን ለሚያመርቷቸው ምርቶች የሀገሪቱን ጥሬ እቃዎችና የሀገሪቱን የሰው ሃይል በከፍተኛ ደረጃ የማይጠቀሙባቸው ከሆነና ለሚቀጥሯቸውም ኢትዮጵያውያን ለኑሮዋቸው በቂ የሆኑ ክፍያዎችን የማይከፍሉ ከሆነ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገትና እርስ በእርስ መደጋገፍ (backward and forward economic linkages) አመርቂ

አስተዋፅኦ የማያደርጉ የውጭ በዝባዥ ካፒታሊስት አገሮች የብዝበዛ ወኪሎች የሆኑ "ደሴቶች" ብቻ (enclave economies) ከመሆን እንደማያልፉ መታወቅ አለበት። ለሀገራችን አስተማማኝ፣ ተጨባጭና ዘላቂ አስተዋፅኦ የሚያደርጉት የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች መሆናቸው እግንዛቤ ውስጥ ገብቶ እነዚህን በከፍተኛ ደረጃ መንከባከብና ማበረታት አማራጭ የሌለው ግዴታችን መሆን አለበት።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ ከቅርብ አመታት ወዲህ በተከሰቱት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች የተነሳ የፖለቲካ ስርአታችንን (political system) እንደገና መቃኘት የማይታለፍ አማራጭ ይሆናል፣ የዘውግ ፌደራሊዝም፣ የጥምረት አውራፓርቲና አገዛዝ (government)፣ የመገንጠል መብት፣ ወዘተ ከተማከለና አንድወጥ አመራር ጋር ሊታረቁ አይችሉምና ። ነገር ግን ገዥው ፓርቲና አገዛዙ ተአምራዊ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ለማስገኘት የዛሬው የአለም የኢኮኖሚና የንግድ ሥርአት የማይፈቅድ እንዲሁም የተከተለው እስትራቴጂና ፕሮግራም ከጊዜ በሁዋላ በከፍተኛ ደረጃ የህዝብ ተቃዉሞ የጋበዘ (ከ2008—2010 አም በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ክልል፣ በኢትዮጵያ ሱማሌ፣ ወዘተ የተቀሰቀሱትን ህዝባዊ አመፆችን ያስታውሷል) አካሄድ ከመሆኑም በላይ እስከዛሬ የነበረው ጉዑት ከምኞት በላይ የማያስኬድ የህልም እንጀራ ነው ብሎ በቁርጠኝነት ለማመን ከተገደደና ካሉት ተቃዋሚዎች ጋር በሰላማዊ መንገድ ለመወዳደር፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫዎችን ለማካሄድ፣ የመራጩን ህዝበ—ውሳኔ ለማክበርና እንደነኮሪያ፣ ታይዋን፣ ሲንጋፖር (የሩቅ ምስራቅ እስያ) ወይም እንደቦትስዋና፣ ጋናና ደቡብ አፍሪካ(አፍሪቃ) ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ የመንግስት ሞዴል (democratic developmental state) ለመከተልና በዚሁ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ለማስረጽ፣ ነፃትንነና ሰብአዊ መብትን ለማረጋገጥ፣ የህግ የበላይነትና ፍትህ የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ርአት ለመገንባት ቁርጠኛ የፖለቲካ ውሳኔ አድርገናል የሚሉ ከሆነ አሁን ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የተጀመረው ውይይትና ድርድር በሚያስተማምን ሁኔታ ቀጥሎ ሁሉንም የአገሪቱ የወደፊት እጣ ፈንታ ያገባናል የሚሉ ሃይሎችን ሁሉ ወደሚያግባበ ዘላቂ የእልባት ምእራፍ ማሸጋገር አማራጭ የሌለው አቅጣጫ ይሆናል። ኢትዮጵያ ከ1987 አም አንስቶ ባፀደቀችው ህገመንግስት የተቀበለችው የብዙሃን ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርአትና ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ መንግስት እንደመሆኑ መጠን የዘውግ/የቋንቋ ፌደራሊዝም አወዛጋቢ መሆኑ ባይካድም የፌደራሊዝም ስርአት የሚያዋጣት አማራጭ ስለመሆኑ አንዳችም ጥርጣሬ የለኝም። ለዚህም እውነታ ኢህአዴግ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲያበቃቸው መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን።

በመጨረሻም ሁላችንም ኢትዮጵያውያን (በአገር ውስም ሆነ በውጭ አገሮች የምንኖር ዜጎች) አገራችንና ህዝባችንን በተመለከተ በተለያዩ መድረኮችና ሚዲያዎች የምናካሂዳቸው ውይይቶችና ክርክሮች ከስሜታዊነት፣ ከጥላቻና ከዘረኝነት የፀዱ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄዎችን የምናደርግበት ወቅት መሆኑን ማጤን የግድ ይለናል። በአንድ ወቅት Learned Hand (ሌርንድ ሃንድ) የሚባሉ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍረድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ፣ "በተመልካቾች ብዛት የተነሳ እጅግ በተጨናነቀቀ ቲያትር ቤት ውስጥ፣ እሳት! እሳት! ብሎ መጮህ ታላቅ ወንጀል ነው፣ ከዚያ አደጋ ለማምለጥ ሲል ታዳሚው የነፍስ አድን ትግል ሲያደርግ ከሚያስከትለው የመረጋገጥ፣ የመቁሰልና የመሞት አደጋ ባሻገር በንብረት ላይ የሚደርሰው ጥፋት ከፍተኛ ይሆናልና"፣ ሲሉ እንዳስጠነቀቁት ሁሉ ካለፉት ጥቂት አመታት ወዲህ (ከ2008 አንስቶ እስካሁን) ኢትዮጵያም እንደተባለው የተጨናነቀች የቲያትር ቤት የሚያስጨንቅ የፖለቲካ ድባብ የሚያንዣብብባት ሀገር ስለሆነች፣ በማናቸውም ሚዲያ (መደበኛም ሆነ ማህበራዊ ሚዲያ) ላይ የምንፅፈውም ሆነ በየትኛውም መድረክ የምንናገረው ሁሉ የግለሰቦችን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ለማስጠበቅ ከመጣር ይልቅ የህዝባችንንና የአገራችንን ደህንነት የሚያስቀድምና ያንዣበበብንን ይህንን አሳሳቢ ተግዳሮት ያገናዘበ እንዲሆን ወገኖቻችንን ሁሉ እንማፀናለን። የወደፊቷን ዘመናዊት ኢትዮጵያን በአ ንድነት ለመገንባት የምንሻ እንደመሆናችን መጠን፣ የአመፅ አማራጭና በዘረኝነት ላይ የተመረኮዘ የእርስ በእርስ ጦርነት ለምንወዳት አገራችንና ህዝባችን የጥፋት እንጂ የእድገት፣ የደህንነትና የልማት መንገድ እንደማይሆን በአፅንኦት ለማስገንዘብ እሻለሁ። ሰላማዊ የትግል አማራጮች ሁሉ ካልተዘጉብን በስተቀር ለአገራችን የምንመርጠው የትግል አማራጭ የሰላምና የሰላም መንገድ ብቻ እንዲሆን ወገኖቻችንን እንማፀናለን። በመንግስታችን የአመራር ጉድለትና በህዝቦቻችን የእርስ በርስ ግጭቶች የተነሳ የጋራ ቤታችንና ዞሮ መግቢያችን እንዳትፈራርስ ብርቱ ጥንቃቄዎችን ካላደረግን የዛሬዎቹ ሊቢያ፣ የመን፣ ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ አፍጋኒስታን፣ ወዘተ ካለፉት ሁለት አስርተ አመታት ወዲህ እየደረሰባቸው ያለው ፍጅትና ውድመት ሊደርስብን

አይችልም ብለን መዘናጋት አጉል የዋህነት ይሆናልና ልብ ያለው ልብ ይበል። እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ልጆቿን ይባርክ፣ ይጠብቅ።

**ከድልበቶ ደጎዬ ዋቆ፣**

ትግራዋዩ ለአማራው፣ አማራው ለኦሮሞው፣ ሱማሌው ለአፋሩ፣ አርጎባው ለሀረሪው፣ ሀዲያው ለከምባታው፣ ስልጤው ለጉራጌው፣ ወላይታው ለሲዳማው፣ ጌዴኦው ለጉጂው፣ ጋሞው ለዳውሮው፣ ቤኒሻንጉሉ ለጋምቤላው፣ ሃላባው ለማረቆው፣ ቀቤናው ለመስቃኑ፣ ቅማንቱ ለሽናሻው፣ ከፍቾው ለሸክቾው፣ ቡርጂው ለአማሮው፣ ኮንሶው ለቦረናው፣ ወዘተ ሁሉም ለሁሉም፣ ጠላቱ ሳይሆን ጥላው፣ ስጋቱ ሳይሆን ስጋው ነው። ይህንን ከአያት ቅድመአያቶቻችንና ከተለያዩ የሃይማኖት ሲኖዶሶችና ቀኖናዎች ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፉ አያሌ ዘመናትን ያስቆጠሩ የተከበሩ የጋራ፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ውርሶችና እሴቶችን ዘንግተን እንዴት የጥላቻ፣ የዘረኝነትና የጦርነት ዘመቻ በገዛአገራችን ህዝቦችና ሃይማኖቶች መካከል እናሰራጫለን፣ እናራግባለን? እንዴት እንዴት የጋራ ራእይ፣ የእርስ በእርስ የመደጋገፍና የመተሳሰብ የጋራ ታሪክ ላሽቆ ወደየጎሳችንና ወደየጎጣችን ድንኳን ወርደን ለመወሸቅ እንመርጣለን? አሳዛኝ ውድቀት ነው፣ አሳፋሪ ዝቅጠት ነው፣ ወገኖቼ! እንዴትስ የመላው አለም ህዝቦች ከበሬታና አድናቆት እየተቸረን አያሌ ዘመናትን ያሳለፍን ጥንታዊ ሀገርና ህዝብ ዛሬ በድንገት ለአለም ህብረተሰብ የትዝብት፣ የስጋትና የንቀት ኢላማ ለመሆን እንሽቀዳደማለን? ይህንን የሚያንዣብብንን ስጋትና አደጋ በፅናት ለመቋቋም ከእንቅልፋችን ነቅተን በተባበረ መንፈስ እንጋደል።

የአገሬ ህዝብ ሆይ፣  የጥላቻ ንግግር፣  ዘረኝነት፣ የሃይማኖትና የብሄር አክራሪነትና ፅንፈኝነት ጥዩፍ ናቸው፣ የጥላቻ ንግግርና ዘረኝነት የጠነቡና ህገወጥ የሆኑ አስተሳሰቦች ናቸው፣ የሩዋንዳ የዘር ፍጅት ታሪክ በሀገራችን እንዲደገም የሚሹ ፅንፈኛ የሃይማኖትና የብሄር ቡድኖች እያራገቡና እያቀጣጠሉት የሚገኝ የእርስ በእርስ የእልቂት ግብዣ ነው።

ወገን ሆይ፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከተሸበብክበት የፍርሃትና የስንፍና ቆፈን ተላቀቅ፣ ንቃ፣ ሁሉ ነገር ከወደመ በሁዋላ ከመቆጨት በጊዜ የማይቀረውን ፍልሚያ ለመጋፈጥ ዛሬውኑ ተነስ! ቡራዩ፣ ሰበታ፣ ለገጣፎ፣ ሃዋሳ፣ ጌዴኦ፣ ኮሬ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ ካፋ ዴቻ፣ ኮንሶ፣ ዳውሮ ተርጫ፣ ጉራፈርዳ፣ ሸካ ሸክቾ፣ ማጂ ቴፒ፣ አጣዬ፣ ከሚሴ፣ ማጀቴ፣ ወሎ፣ ምእራብ ወለጋ፣ ወዘተ የተፈጸሙት የወገኖቻችን መፈናቀል፣ ለችጋርና ለሰቆቃ መዳረግ፣ በጅምላ መገደል፣ የአብያተክርስቲያናትና የቀሳውስት መቃጠል፣ ወዘተ በየጊዜው እየተዘወተረ እንዳለ እየታዘብክና በራስህና በቤተሰብህም ላይ እያነጣጠረ እየተመለከትክ ምን እስኪሆን ነው ተኝተህ የምታንቀላፋው? በህይወት የመቆየት የህልውና ጥያቄ ጭምር አጠያያቂ በሆነበት በዚህ አስጊና አስከፊ ወቅት አደጋው ደጅህን እስኪያንኳኳ ድረስ መጠባበቅ የለብህም። ጊዜው አሁን ነው፣  ከጥላቻ፣ ከብሄርና ከሃይማኖት አክራሪነት እንዲሁም ከዘረኝነት እንራቅ፣ እነዚህን መርዘኛ አስተሳሰቦችን በማራገብና በመተግበር ላይ የተሰማሩትን የሃይማኖትና የብሄር—ተኮር ፀረ—ህዝብ ሃይሎችን ለመደምሰስ ሌት ተቀን በአስተሳሰብና በትጥቅ ጭምር  ለመታገልና ድል ለመንሳት ታጥቀን እንነሳ፣ አገርና ህዝብ የሚያወድሙ አስተሳሰቦችና ሃይሎች ናቸውና። ሰላማዊ አብሮነታችን ይለምልም ዛሬም፣ ነገም፣ ለተነገወዲያም፣ ለዘለአለምም!! እግዚአብሄር ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን በፅኑ ሰላምና በማይናወጥ አንድነት ይጠብቅ፣ ይባርከን።